# ምርጫ መጣ፣ ረበሻ ውጣ

ክፍል አንድ

ኢብሳ ነመራ

09-18-14

2007 ዓ/ምን ከተቀበልን ቀናት ተቆጥረዋል። ይህ ዓመት አምስትኛው ዙር ሃገራዊ ምርጫ የሚካሄድበት መሆኑ ከባለፉ አራት ዓመታት ልዩ ያደርገዋል። ዘንድሮ የሚካሄደውን አምስተኛ ዙር ምርጫ አስመልክቶ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መልዕክት አስተላልፈዋል። የኢህአዴግ ምክር ቤት በጷግሜን ወር ውስጥ ያካሄደውን ሥብሰባ ሲያጠናቅቅ በሰጠው መግለጫ፣ የሃገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ሉዐላዊ የሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጫ በሆነው ለአምስተኛ ግዜ በሚካሄደው ሃገራዊ ምርጫ ኢህአዴግ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት የሚያስችለውን የምርጫ ስትራቴጂና ዕቅድ ገምግሞ ማፅደቁን አሥታውቋል።

ኢህአዴግ በመጪው ምርጫ ላይ ድርብ ድርሻ ነው ያለው። አንደኛው እንደማንኛውም ሕጋዊ ሆኖ እንደሚንቀሳቀስ የሃገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲ ያለው ድርሻ ሲሆን፣ ሌላኛው እንደገዢ ፓርቲ ያለው ድርሻ ነው። እንደ ገዢ ፓርቲ ወይም እንደመንግሥት ምርጫው አሳታፊ፣ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተዓማኒ እንዲሆን በመስራት ረገድ ድርሻ አለው። በሌላ በኩል በዚህ ምርጫ ውስጥ እንደ አንድ የሃገሪቱ ፓርቲ አማራጭ ፖሊሲዎቹንና አቋሞቹን እያስተዋወቀ የሥልጣን ውክልና ለማግኘት ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ይፎካከራል።

ምንም እነኳን የምርጫ ጉዳዮች የበላይ ኃላፊ ከመንግስት ገለልተኛ የሆነው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ቢሆንም፣ ኢህአዴግ በህዝብ ውክልና ሥልጣን ላይ በቆየባቸው ያለፉ ዓመታት እንደገዢ ፓርቲ በመላው ሃገሪቱ ሰላማዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች እንዲካሄዱ በማድረግ ረገድ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ተወጥቷል። ሰላማዊ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ ረገድ የሰፋ ተሞክሮ አለው።

ምርጫን በማስታከክ ከህዝብ ውክልና ውጭ የመንግስትን ሥልጣን ለመመንተፍ የተሞከረበትን በምርጫ 97 ማግሥት የተከሰተውን የሁከትና የግርግር ፈተና አልፎ የህዝብን ሥልጣን ማስከበር መቻሉ ስልጣን በቀላሉ በማንም እንዳይነጠቅ የመከላከል ብቃቱ አስተማማኝ መሆኑን አረጋግጧል። በመሆኑም መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በማድረግ የህዝቡን ብቸኛ የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት የማረጋገጥ ኃላፊነቱን በብቃት ይወጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ኢህአዴግ እንደ አንድ ሕጋዊ የሃገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲ የሚኖረው ተሳትፎም ላይ እጅግ ብርቱ ተፎካካሪ መሆኑን ከወዲሁ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ፣ የሉዐላዊ ሥልጣን ባለቤት ሆነው እርስ በርስ በመከባበር ላይ በተመሰረተ እኩልነት መኖር የቻሉበትን ፌደራላዊ ሥርአት በመፍጠር ሂደት ውስጥ የጎላ ታሪክ ያለው ፓርቲ ነው። ኢህአዴግ የብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን ብሄራዊ መብትና ነፃነት የተቀበለና መብትና ነፃነታቸውን እንዲያጣጥሙ የሰራ፣ አሁንም ይህን በተጠናከረ ሁኔታ ማስቀጠል የሚያስችል ፖሊሲ ያለው፣ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች የቃል ኪዳን የሆነውን ሰነድ ማክበርና ማስከበር መለያው ለመሆን የበቃ ፓርቲ ነው። በዚህ ምክንያት እጅግ ሰፊ ሕዝባዊ መሰረት አለው።

ከዚህ በተጨማሪ በህዝብ ውክልና ሥልጣን ላይ በቆየባቸው ያለፉ ሁለት አስርት ገደማ ዓመታት በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች ያስመዘገባቸው  ተጨባጭ ውጤቶች ኢህአዴግ የህዝቡን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችል ፖሊሲዎች ያሉት መሆኑን፣ ፖሊሲዎቹን የማስፈፀም ብቃት ያለው ፓርቲ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች የተመዘገቡት እድገቶች በገለልተኛ ዓለም አቀፍ ተቋማትና መንግስታት ጭምር የተመሰከረ ነው። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ በተለይ ለተቀሩት የአፍሪካ ሃገራት በሞዴልነት የምትወሰድ ሃገር ለመሆን መብቃቷንም ልብ በሉ።

በሌላ በኩል ከዚህ ሰፊ ህዝባዊ መሰረት ካለውና ሃገሪቱን የመምራት ብቃቱን በተግባር ካረጋገጠው ኢህአዴግ ጋር የሚፎካከሩት የሃገሪቱ ፓርቲዎች አቅም፣ አደረጃጀትና አቋም በነፃና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ መንቀሳቀስ የሚያስችላቸው አይደለም።

‘ሁሉም’ ማለት በሚቻልበት ደረጃ የሃገሪቱን ነበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያገናዘበ የጠራ ፖሊሲ፣ ግልፅ የሆነ የሰላማዊ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ስትራቴጂ፣ ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዲሁም  ዓላማ ያለው አባል የላቸውም። በየወቅቱ ይህን አቅማቸውን የማጠናከር እርምጃ ሲወስዱም አልታዩም።

በተለይ በፌደራል ደረጃ የሚንቀሳቀሱት ‘አይነ ግብ’ ነን የሚሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሰረት የሆነውን የኢትዮጵያ ብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን ብሄራዊ መብትና ነፃነት የተቀበሉ አይደሉም። አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚወክለውን አርሶ አደር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶችና ጥቅሞች መሰረት ያደረገ ኢኮኖሚያዊ ፓሊሲዎችም የላቸውም። በመሆኑም ሕዝባዊ መሰረት አልገነቡም።

አብዛኞቹ ‘አይነ ግብ’ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦቹና ሕዝቦችን ብሄራዊ መብትና ነፃነት የሚያረጋግጡ እንዲሁም አብዛኛውን ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅና ይህን ይዞ ወደሕዝብ ለመዝለቅ ሲነቀሳቀሱ አልታዩም።

ከዚህ ይልቅ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በየወቅቱ ብልጭ የሚሉ ቀልብ የሚሰቡ አጀንዳዎችን ያለወጉ በማራገብ አንድ ሰሞን ቦግ ብሎ የሚጨልም የህዝብ ድጋፍ ላይ ሲዋዢቁ ነው የሚታዩት። አንድ ሰሞን አንዱ ‘ሆይ፣ ሆይ’ ብሎ ይሰወራል። ሌላ ግዜ ደግሞ ሌላው እነዲሁ ቀልበ ሳቢ ወቅታዊ አጀንዳ ይዞ ይነሳና ‘ሆይ፣ ሆይ’ ብሎ ይሂዳል። ከዚህ ያለፈ ሰፊ ሕዝባዊ መሰረት እንዲኖራቸው የሚያስችላቸው ዘላቂ ሥራዎችን አከናውነው አያውቁም። ከዚህ በተጨማሪ የውስጥ ችግሮቻቸውን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍታት እየተሳናቸው አልፎ አልፎ እስከ ድብድብ የሚዘልቅ ድብድብ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ነው የሚስተዋለው።

እንግዲህ አምስተኛውን ዙር ሃገራዊ ምርጫ የምናካሂደበትን 2007 የተቀበለነው በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ነው። ታዲያ የ2007 አዲስ  ዓመት በግባትን ምክንያት በማድረግ ከምርጫ ጋር የተያያዘ መልዕከቶችን ያዘሉ መግለጫዎች ያወጡ ፓርቲዎችን አድምጠናል፤ አንብበናልም። በመግለጫ መልዕክት ካስተላለፉ ፓርቲዎቸ መሃከል ‘አይነግቡ’ አንድነት

ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ - አንድነት ይገኝበታል። አንድነት በመግለጫው፣ የፓረቲውን የምርጫ ዝግጅት የሚመለከትና ተያያዥ ጉዳዮችን ያነሳ በመሆኑ በዚህ ፅሁፍ ልመለከተወ ወድጃለሁ።

አንድነት ጳግሜ ወር ውስጥ 2007 አዲስ ዓመት መግባትን አስመልክቶ በፅህፈት ቤቱ በሰጠው መግለጫ ባስተላለፈው መልዕክት፣ "በአዲሱ ዓመት ሃገራዊ ኃላፊነትን ለመሸከም ተዘጋጅቻለሁ።" በኋል። ይህ የአንድነት መልዕክት እውነት ከሆነ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅ በመሆኑ የሚደገፍና አበጀህ የሚያስብል ነው።

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በመስራቾቹ፣ በአመራሮቹና አባላቱ ጥቅምና ፍላጎት የታጠረ መሆን የለበትም። ከዚህ ይልቅ የህዝብን መብቶችና ነፃነቶች፣ ፍላጎቶችና ጥቅሞች ማረጋገጥና ማስከበርን መድረሻ አድርጎ መመስረትና መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። በመሆኑም አንደነት ፓርቲ "በ2007 ሃገራዊ ሃላፊነት ለመሸከም ተዘጋጅቻለሁ" ማለቱ ተገቢ ነው።

በዚህ "የህዝብን ኃላፊነት ለመሸከም ዝግኝት አድርጌበታለሁ" ባለበት ዓመት የህዝብን መብቶችና ነፃነቶች፣ ፍላጎቶችና ጥቅሞች ማስከበርና ማሟላት የሚችሉ ፖሊሲዎችን ካልቀረፀና ለሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ቁርጠኛ ካልሆነ ዋጋ የለውም። በእስከዛሬው አካሄዱ ይህን ስላላሳየ አሁን ድንገት "ሃገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ተዘጋጅቻለሁ" ማለቱ ብቻውን እውነት ዝግጅት ማደረጉን አያመለከትም። በመግለጫው ላይ ያስተላለፋቸው መልዕክቶችም ይህን አያሳዩም።

አንድነት በሰጠው መግለጫ " የገዢውን ፓርቲ 'ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ' አይነት አካሄድ አጥበቄ እቃወማለሁ" የሚል መልዕክት አስተላልፏል። አንድነት ይህን "ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ" የሚለውን አገላለፅ አዲስ ጉዳይ የተሰኘ መፅሄት ላይ ከወጣ ፅሁፍ ነው የተዋሰው። የዚህ ፅሁፍ ይዘት፣ ፅሁፉን ይዞ የወጣውን አዲስ ጉዳይን ጨምሮ በአምስት መፅሄቶችና በአንድ ጋዜጣ አሳታሚዎቾ ላይ የተመሰረተውን ክስ የሚመለከት ነው። ከአንዳንድ የግል ሚዲያ እንደሰማነው፣ የመፅሄቶቹ አሳታሚዎች ላይ ክስ መመስረቱን ተከትሎ የተወሰኑት አሳታሚዎች ሥራአስኪያጆችና ጋዜጠኞች ከሃገር በመኮብለላቸው ህትመታቸው

ተቋርጧል። “ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ” የተሰኘው ሃሳብ ይህን የፕሬሶቹን ህተመት መቋረጥ በማሰመልከት የወጣ ነው።

በዚህ ዙሪያ ያለውን እውነታ ስንመለከት እርግጥ ነው የአሳታሚዎቹን መከሰስ ተከትሎ የአብዛኞቹ ህትመት ተቋርጧል። የተቋረጠው አሳታሚዎቹና ጋዜጠኞቹ ሥራ በማቋረጣቸውና ምናልባትም ከሃገር በመኮብለላቸው ነው። የመፅሄቶቹ አሳታሚዎቹና አዘጋጆች ‘ከሃገር ኮብልለዋል’ የሚለውን ወሬ የሰሙ አታሚዎች/ማተሚያ ቤቶች መፅሄቶቹን አትመው ለስርጭት ዝግጁ ማድረጋቸው በተዋረድ ወደሕግ ተጠያቂነት እንደሚወስዳቸው ያውቃሉ። በዚህ ሳቢያ ለማተም ፍቃደኛ ያልሆበት ሁኔታ ይኖራል ተብሎ የገመታል።

ከዚህ ውጭ ፍትህ ምኒስትር፣ ፍርድ ቤት ወይም የፕሬስ አሰራር ጉዳይ የሚመለከተው ሌላ መንግሥታዊ ተቋም የመፅሄቶቹና የጋዜጣው ሕትመት እንዲቋረጥ ውሳኔ አላሳለፈም። በመሆኑም እስካሁን ባለው ሁኔታ መሥሄቶቹ በመንግስት ውሳኔ የተቋረጡ አሰመስሎ ማቅረብ የህግን አግባብ ያልተከተለ ነው። አናም ተገቢ አይደለም።

በሌላ በኩል፣ ሁላችንም እንደምናውቀው፣ የአንድነት አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር እነደሚያውቁት አሳታሚዎቻቸው ላይ ክስ የተመሰረተባቸው አምስት መፅሄቶችና አንድ ጋዜጣ ነፃ ፕሬሶች አይደሉም። ከዚህ ይልቅ የተወሰነ ቡድን የፖለቲካ አመለካከት አራማጆች (advocates) ናቸው። እነዚህ ፕሬሶች ሁሉም አመለካከቶች በእኩል የሚስተናገዱባቸው፣ ሚዛናዊ መረጃዎች የሚወጡባቸው ሳይሆኑ ለአንድ ወገን አመለካከት የበላይነት የሚሰሩ ናቸው።

መፅሄቶቹ የሚያራምዱት አመለካከት ደግሞ ከህዝብ ውክልና ይልቅ ሕገመንግስታዊውን ሥርአት በኃይል በመናድ ስልጣን መቀማትን ዓላማ ያደረገ አመለካከት ነው። ይህን ማወቅ ልዩ ጥናት የሚፈልግ አይደለም። መፅሄቶቹ ይዘዋቸው ይወጡ በነበሩ ፅሆፎችና የአዘጋጆቹ አቋም በሚንፀባረቅባቸው ርዕሠ አንቀፆች ላይ በይፋ ታይቷል። ይህን የማያውቅ ካለ የመፅሄቶቹ የኋላ እትሞች አሁንም አልፎ አለፎ እየተሸጡ ሥለሆነ ገዝቶ መመለከት ይችላል።

እነዚህ መፅሄቶች ህገመንግስታዊውን ሥርአት በኃይል የመናድ አመለካከተ አራማጅ መሆናቸው ላይ በተቃዋሚዎችና በመንግስት እንዲሁም በህዝቡ መሃከል ተመሳሳይ አቋም ነው ያለው። ህገመንግስታዊውን ሥርአት በኃይል የመናድ አመለካከት እንደሚያራምዱ ሁሉም ወገኖች ይስማማሉ። ልዩነት ያለው ይህ የሚያራምዱትን አቋም በመደገፍና ባለመደገፍ ላይ ነው። የተወሰኑ ቡደኖች የመፅሄቶቹን አካሄድ ይደግፋሉ፤ መንግስትን ጨምሮ ሌሎች ወገኖች ደግሞ አካሄዱን ይቃወማሉ፤ በቃ።

እነዚህ ሕገመንግስታዊ ሥርአቱን በኃይል የመናድ አመለካከት አራማጅ የነበሩ መፅሄቶች፣ ይህን ዓላማቸውን ለማሳካት መጪውን ምርጫ እንደመልካም አጋጣሚ ወስደውታል። አንዳንዶቹ “የህዳሴ አብዮት” በለው በሰየሙት አመፅ የህዝብ ውክልና ሳያስፈልግ ሥልጣን የመመንተፍ እንቅስቃሴ ለማደረግ በይፋ ጥሪ አስተላልፈዋል።

እንግዲህ አሳታሚዎቹ ላይ ክሥ መመስረቱ ከዚህ በፊትም ሲደረግ እንደቆየው ህግ የማስከበር እርምጃ እንጂ ምርጫው መቃረቡን ምክንያት በማድረግ የተደረገ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተከሰሱበት ግዜ ከምርጫ መቃረብ ጋር መገጣጠሙን የሚገልፀው አባባል “ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ” የሚለው ሳይሆን “ምርጫ መጣ ረብሻ ውጣ” የሚለው ሆኖ እናገኘዋለን። መፅሄቶቹ መጪውን ምርጫ በኃይል ሥልጣን ለመመንተፍ እንደመልካም አጋጠሚ መውሰዳቸው፣ በቸኛ የመንግስት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ መፅሄቶቹን ሥርአት ለማስያዝ የተወሰደውን ይህግ እርምጃ ከምርጫ መቃረብ ጋር መገጣጠሙን “ምርጫ መጣ፣ ረብሻ ውጣ” በሚል ነው የሚገልፀው።